ዳግማዊ አጤ ምኒልክ አሃጉራዊ ጀግና እና ዘለዓለማዊ የነፃነት ሃውልት ናቸው።



HIS IMPERIAL MAJESTY, MENELEK II., EMPEROR OF ABYSSINIA AND KING OF SHOA.

የዳግማዊ አጤ ምኒልክን ግዙፍ ታሪካቸውን እና ድርብርብ ጀግንነታቸውን ማክበር እና ማስክበር የኢትዮጵያ ታሪክ በመሆኑ ከእያንዳንዳችን የኢትዮጵያ ዜጎች የሚጠበቅ ነው። እባካችሁ የካቲት 23 በመጣ ቁጥር የአደዋን በዓል ስታከብሩ በአደዋ ዳግማዊ አጤ ምኒልክ ዘኢትዮጵያ ያስመዝገቡት የማይታጠፍ ጀግንነት ከኢትዮጵያ አልፎ የአፍሪካ አሁጉር ታሪክ መሆኑን እና እንደውም አልፎ ተርፎ የአለም ታሪክ ስለሆነ ይሄንን በመረዳት በመረጃ በዚህ መልክ በአለም ዙሪያ በዩንቨርስቲው ውስጥ ሁሉ የሚሰጥ እና ሲሰጥም የኖረ መሆኑን ተረድተን የኢትዮጵያ ብቻ አድርገን ኢትዮጵያዊ ለኢትዮጵያዊ ብቻ ከመጠራራት ኢትዮጵያዊ ያልሆኑትን ሰዎች ሁሉ በመጋበዝ ፡ ትናንትና ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ አብራክ በወጣው ሰራዊ የተገኘውን ነጻነት ወያኔውች ክደው መረብን ለጣሊያን መንግስት አጤ ምኒልክ ሳያውቁ በመስማማት በመሸጣቸው በመቸረሻ የአደዋን ጦርነት መክኒያት የሆኑት እራስ መንገሻ ዮሐንስ የአጤ ዮሐንስ ልጅ ለግል

ለስልጣናቸው ብለው ትግራይን እና ሕዝብዋን ሸጠው እንደነበረ አስተምሩ። የአደዋን ጦርነት ዳግማዊ አጤ ምኒይልክ ያመጡት ወይም የጫሩት አይደለም ወያኔ እንደሚያናፋው። ተከታዮቹም የታሪክ ደሆች በመሆናቸው ራስ መንገሻ ዮሐንስን ነው ነፃአውጪ አድርገው የሚያወድሱት።

ሃቁ ግን በታሪክ ተመዝግቦ ከ40 መጻሃፍት ያላነሰ ይዞት ከለው እንክዋን ብናይ የራስ መንገሻ ዮሐንስ አሳፋሪ ክህደት እና አገር መሸጥ ጀግናውን አሉላ አባነጋን ሁሉ አሳምነው ለጣሊያን ገብተው እንደነበረ የማይካድ ታሪክ እና በእጃችን የሚገኝ ታሪክ ነው።

አጤ ምኒልክ የአደዋን ጦርነት ያመጡት አይደለም።

ይልቅስ ያደረጉት በተለይ ለትግራይ ሕዝብ በጭንቀት ውስጥ ለወደቀው ደርሰው ባጭሩ ከጣሊያን መንጋጋ ውስጥ በራስ መንገሻ ገብቶ የነበረውን የትግራይን ሕዝብ እና ትግራይን እራሳቸው እራስ መንገሻ ዮሐንስን ጭምር ጣሊያን እያላመጣቸው ስለነበረ ሳይሰለቅጣቸው በፍጥነት ጣሊያንን እረፍረፈው ከመንጋጋው እና ከላንቃው ትግራይን እና የትግራይን ሕዝብ መንገሻ ዮሐንስንም እንደከሃዲነታቸው ሳይሆን እንደወንድ ፈረስ ላይ አስቀምጠው አገር ለማዳን እንደወንድ እንዲዋጉ የልብ ልብ ሰጥተው የኢትዮጵያ ወንድ በሃሞት እንዴት እንደሚዋጋ ለአገሩ ክብር እና ለሕዝብ በጦርሜዳ አስተምረዋል አጤ ምኒልክ። ይሄ በስሜት ፡ ወይም በማዳላት ፡ ወይም ከኪስ በማውጣት የሚባል ሳይሆን ሃቁን ጣሊያን እና በተለይ ሳያዳሉ ፈረንሳዮች ጦርነቱን አስመልክቶ የጻፉትን ጣሊያን በአፍሪካ በሚል ማንበብ ይቻላል።

አጤ ምኒልክ

የአውሮፓ ጀነራሎች ለሽላሽ በራሳቸው በጣሊያኖቹ መሳርያ። አጤ ምንይልክ አውሮፓውያንን ማራኪ አንበርካኪ ብቸኛው አፍሪካዊ ናቸው።

የበርሊን ኮንፍራንስ በ1884 ተጀምሮ ከአንድ አመት በኋላ አልቆ 14 መንግስታት በአፍሪካን እንደ አንበጣ ለመውረር በተነስቡት ጊዜ ሌሎች ጀግኖች የአፍሪካ ንጉሶች እና ንግስቶች ንግስቶች ስል እራሳቸውን የአሉ አገር መሪዎች ማለት ነው በተለይ በመራብ አፍሪካ መሪሴቶች በጣም ሰፎ አገር ይዘው ይመሩ ስለነበረ ያለባል ማለት ነው አገርን በማስቀደም ጦርነት ላይ ያተኩሩ ነበር። ለዛሬ ባጭሩ የአፍሪካ መሪዎች አውሮፓውያንን ጀርመንን ፡ ፓርቱጋል ፡ ፈረንሳይ ፡ እንግሊዝ ፡ ጣሊያንን በአራቱም የአፍሪካ መአዘን እስከ ሱዳን ቢዋጉም የጦር ስልታቸው የዳግማዊ አጤ ምንይልክን ማልትም የአጤ ቴዎድሮስ ስልትን ያዘው ስላልነበራቸው ሕዝባቸውን አንድ አድርገው ሊዋጉ ያልቻሉበት ሁኔታ ነበር። እዚህ ላይ ማለት የምፈልገው ሌላው አፍሪካዊ እና ንጉሶቹ አፍሪካን ለመቀራመጥ አውሮፓውያን በበርሊኑ ኮንፈራንስ መስማማት መመርያ አወደ አፍሪካ ሲገቡ እጁን አጣምሮ የተቀበላቸው አፍሪካዊ እንዳልነበረ እና እስከመጨረሻ መዋጋታቸውን እንድንገንዘብ እና እንድንኮራበትም ይገባል መከኒያቱም ያም ታሪካችን ነው። በእርግጥ ማን እንደ አጤ ቴዎድሮስ ለጥቁር ሕዝብ እፍረት እንዳይተውልን እራሳቸውን እንግሊዞቹ የአለም አንድነት መርዞቹ ፊት ጠጥተው በክብር ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተውናል ። ሆኖም አጤ ቴውድሮስ እና አጤ ምኒልክ አጤ ዮሐንስም በመሃላችን ሁሌም አሉ።

ከዚህ በታች በሚኒልክ የተለሸለሸው አሰቃቂ የጣሊያን ሰራዊት መሃል ባለመዳሊያ ደርዳሪ ሃሞተቢስ ሰላቶዎችን (ሶልዳቶ= ወታደር)ሁለት ጀነራሎች አደዋ የሞቱትን እና የተማረከውን እናም ጣሊያን ሁኖ ሌላ መዳሊያ ለመስጠት ይጠባበቅ የነበረውን መሪያቸውን እና የአደዋን ጦርነት

ሊያሸንፍ አቆብቁቦ የነበረውን ወንድ በተፈጥሮ ብቻ ተመለከትዋቸው ለማታውቁዋቸው በዚህ መልክ ማለቴ ነው ።

ታግለው በመቸረሻ ከተማረኩት የአፍሪካ ጀግኖች መሃል ጥቂቶቹ በጣም የምኮራባቸውን ከዚህ በታች እነሆ።

ኢትዮጵያ ለከርሳችን በማንገዛው ልጆችዋ ተከብራ ለዘለዓለም ትኑር።

ከአክብሮት ጋር

የኢትዮጵያወርቅ (የሐረርወርቅ) ጋሻው።





የኢጣሊያ ንጉሥ ኡምቤርቶ ቀዳማዊ
ከፍራቴሊ ትሬቨስ መጽሐፍ



በዓድዋ ጦርነት ላይ የሞተው ጀኔራል ዳቦርሚዳ
ከማዙኮኒ



በዓድዋ ላይ የሞተው ጄኔራል አሪሞንዲ
ከማዙኮኒ መጽሐፍ



በዓድዋ ጦርነት የኢጣሊያ ጦር ጠቅላይ አዛዥ ጀኔራል ባራቲዬሪ
ኢታሊያ ኢን አፍሪካ ከሚባለው መጽሐፍ



የተማረከው ጄኔራል ማቴዎስ አልበርቶኒ
ከማዘቶኒ መጽሐፍ



Emperor Almamy Samory Touré

**እኚህ ንጉስ አፍሪካ በአውሮፓውያን እጅ እንዳትወድቅ ያላደረጉት ትግል የለም ምንም እንኳዋን ቢያዙም መጨረሻ ላይ ፤ የአፍሪካ ታሪክ እናም የአለም ታሪክ በሚገባ ታሪካቸውን የመዘገበላቸው ጀግናችን ናቸው።**

# LEGEND OF NYABINGHI AND THE FIGHT AGAINST EUROPEAN COLONIALISM IN EAST AFRICA

During the European colonial era, Africans from all across the continent fought back to expel these downpressive forces, in order to regain their rightful independence from exploitation and tyrannical rule. A notable anti-colonial resistance movement, led by a lady named Muhumuza (also spelled Muhumusa), took place in the early 20th century in south-western Uganda. Muhumuza is seen as one of the many fantastic Warrior Queens in African history.



A rare picture of Muhumuza (centre)

FOR MORE INFORMATION VISIT http://exhibitions.nypl.org/africanaage/essay-resistance.html እኚህ ንግስት ደግሞ ቀደም ሲል ንግስት አሚና

በመባል ከፓርቱጋል ዳሆሜ በግማሽ ዛሬ ናይጀርያን ጭምር ነፃ ያወጡትን አይነት ሰፊ የአፍሪካን ምድር ይመሩ የነበሩ የዩጋንዳ ንግስት ናቸው።

አስታውሱ አፍሪካ በተፈጥሮ ሃብት ብቸኛዋ ሃብታም አሃጉር እንደመሆንዋ ሁሉ የጀግኖችም ምድር ናት ያውም የወንድ ወንዶች የበቀሉባት። አፍሪካዊነት ትልቅ ክብር አለው ።በሚቀጥለው ስለ ኢትዮጵያ ንግስቶች ንግስት ጣይቱን ጭምሮ የምጽፈውን ይዤ እስክንገናኝ በሌላ አረስት ለዛሬ እዚህ ላይ አቆማለሁ።